# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከኅብረቱ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

## ሕዝብ ትቶ መደራደር ለመንበርከክ መመቻቸት ነው!

በግንቦቱ የምርጫ ሂደት ሳቢያ ዐይን ላለው ሁሉ ግልጽ የሆነ ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላምና ሕጋዊ መንገድ ያሻውን መንግሥት ለመምረጥ ያለውን መብት ሞቶም ተሰውቶም ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የአገሬ ጉዳይ ያገባኛል፥ ይመለከተኛል፥ እየመከርኩ እየዘከርኩ በፖለቲካው መስክ እሳተፋለሁ በማለት ያሳየው ከፍተኛ ጉጉት ነው:: ከዚህ የተነሳ የአገር ጉዳይ የጥቂት መሪዎች ጉዳይ ሳይሆን የጠቅላላው ሕዝብና በያለበት በዚህ ሕዝብ ውስጥ ተተክለው እየተንቀሳቀሱ የሚያንቀሳቀሱት ቀራጥ ዜጎችም ጉዳይ ነው በማለት ሲዋደቅ በፀረ-ሕዝብ ኃይሎች የአፈናና የወከባ ውርጅብኝ ደርሶበታል:: የንፁሐን ልጆቹ ደም በአደባባይ እንደጎርፍ ፈሷል:: በቅድመ-ምርጫ ወቅት የደረሰው ግፍ አንሶ በልጆቹ ደም የተጎናፀፍኩትን ድል በጥቂት የሥልጣን ጥመኞች በጠራራ ፀሐይ አልቀማም በማለት ሲታገል ለሌላ የወከባ፥ የአፈናና የግድያ ውርጅብኝ ተዳርጓል:: አሁንም በአገሬ ጉዳይ ያገባኛል ብሎ በሚያደርገው ትግል ይኸ ነው የማይባል ግፍ እየተፈፀመበት ነው::

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ለዚህ ሕዝባዊ ድል እውን መሆን የሚጠበቅበትን ድርሻ ሲወጣ ቆይቷል:: አሁንም ከሕዝባችን ጎን ሆኖ እየተዋደቀ ይገኛል:: በግንቦት ምርጫ ሳቢያ ሕዝባችን የተጎናፀፋቸው ድሎች ይከበሩ ስንል እነዚህን ድሎች በጠራራ ፀሐይ በሸፍጥና በአመፅ ለመንጠቅና ለመቀልበስ ከሚፍጨረጨሩ ኃይሎች ጋር የተያያዝነው ተጋድሎ የድል ዋስትናው መጀመሪያውኑ እኛ ራሳችንን ከሕዝቡ ወገን የፈረጅነው ዜጎች ይኸንን የሕዝባችንን በአገሬ ጉዳይ ያገባኛል ብሎ የተንቀሳቀሰበትን የትግል አርማ አክብረን ስንገኝ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም::

ከዚህ ሐቅ በመነሳት የኅብረቱ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሕዝባችንን ድል ለማስከበር የሚደረገው ሕዝባዊ ትግላችንና ይኸንን ትግል ለማራመድ ከኢሕአዴግ መንግሥት ጋር የሚደረግ ማንኛውም ድርድር ከእንግዲህ በኅብረተሰቡ ተጋድሎ ካልታጀበ የተጠበቀውን ፍሬ እንደማይሰጥ ተገንዝቦ ይኸ ድርድር ሕዝቡና በመላው አገሪቱ ተሰራጭተው በመዋደቅ ላይ የሚገኙ ታጋይ ልጆች በሙሉ በንቃት የሚሳተፉበት እንዲሆን፤ ከዚህ ድርድር የሚፈልቅ ማንኛውንም ስምምነት ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ኅብረተሰቡ ባልተቋረጠ ሁኔታ በተጠንቀቅ የሚቆምበት ሂደት መሆን እንዳለበት ጉባዔው በግልጽ ተስማምቶ ወስኗል::

*መጀመሪያ* ትግሉ በፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮች ሳይወሰን በየአካባቢው ከሕዝብ ጎን ሆነው የልብ ትርታውን እያዳመጡ የሚዋደቁ ታጋዮች፥ ለዴሞክራሲና ፍትኅ ከፖለቲካ ውጭ ተደራጅተው በትል ላይ ያሉ የተለያዩ የሙያ ስብስቦች፤ የሴቶች፥ የወጣቶች፥ የገበሬዎች፥ የሠራተኞች ተወካዮች፥ የአገር ሽማግሌዎች፥ ወዘተ.... ጉዳይ መሆኑን ተቀብሎ፥ እነዚህ ሁሉ ኃይሎች መክረውና ዘክረው የግንቦቱን ድሎች ለማስከበር ስለሚደረገው ትግል አገር አቀፍ ስትራቴጂ እንዲነድፉ መስከረም 20 እና 21 ቀን 1998 ዓ.ም. አንድ ብሔራዊ “ የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ” እንዲጠራና ይኸ ጉባዔ በሚነድፈው ስትራቴጂ መሠረት ከኢሕአዴግ ጋር መደራደርን የሚጨምር አዲስ የትግል ምዕራፍ እንዲከፈት፤

ዋና መሥሪያ ቤት/Main Office
ፖ.ሳ.ቁ ጥር 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁ./Tel.: 251-1574719;ፋክስ/Fax) 574720

ሰሜን አሜሪካ/North America
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

ሁለተኛ ከእነዚህ ሁሉ ኃይሎች አልፎ ዋናው የትግሉ ባለቤትና ባለጉዳይ በየዕለቱ በንፁኃን ልጆቹ ደምና እንባ እየከፈለ የነፃነታችንን ችቦ አብርቶ የያዘው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሆኑ ይኸንን በግንባር ቀደም ታጋይ ልጆቹ የሚነደፍ የትግል፥ የዴሞክራሲና የብሔራዊ እርቅ አጀንዳ ደግፎ እንዲንቀሳቀስ መስከረም 22 ቀን 1998 ዓ/ም ከአዲስ አበባ ጀምሮ በመላ አገሪቱ ታላላቅ ከተሞችና በዓለም-አቀፍ ደረጃም የድጋፍ ሰለማዊ ሰልፎች እንዲደረጉ ጥሪ አድርጎ ነበር።

የሕዝባችንን የተደራጀ ትግል እንደ ጦር የሚፈሩት የኢሕአዴግ መሪዎች ይኸ ተጋድሎ በተተራመሰ መልክ እንዲካሄድና በዚህ የእውር የድንብር ጉዞ በቀላሉ እንዲመታ ከአላቸው ሕልም ተነስተው ይኸ ጉባዔ እንዳይካሄድ አደናቀፉ። ከመላ ኢትዮጵያ ተጠራርተው ስለጋራው ትግል ለመምከር አዲስ አበባ ገብተው የነበሩ ዜጎች እንደተመኙት ተወያይተው ስለ ሰላም፥ ስለ ዜጎች አንድነትና ትስስር፥ ስለ ዴሞክራሲ ለምናደርገው ሰላማዊ ትግል አገር አቀፍ የሆነ ስትራቴጂ ማውጣት ሳይችሉ ወደየመጡበት በቁጭትና በፀፀት ተመለሱ። ለዚህ ለአገራችን ሰላም፥ ለሕዝባችን አንድነትና ለዴሞክራሲ ጥሪ ሕዝባችን በያለበት በነቂስ ወጥቶ ያለውን ድጋፍ እንዳያሳይባቸው የሰጉት የኢሕአዴግ መሪዎች ይኸን የማንንም በየትም ቦታ ያለ ሕዝብ የማይገፈፍና በራሳቸው ሕገ መንግሥት የተደነገገ መሠረታዊ መብት በመንፈግ የድጋፍ ሰልፉ እንዳይደረግ ከለከሉ።

ቅንጅቱና ኅብረቱ ይኸን በኢሕአዴግ ግትርነት የተፈጠረ አስጊ የውጥረት ሁኔታ ለማርገብና ሕዝባችንን ለጥቂት የኢሕአዴግ መሪዎች የአመፅ ሴራ ላለማመቻቸት ከአላቸው ፅኑ ፍላጎትና የሃላፊነት ስሜት በመሳት የሰለማዊ ትግላችንን ስልት ቀይረው ከሰኞ መስከረም 23 ጀምሮ እስከ ረቡዕ መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ/ም ድረስ ሁሉም በየቤቱ ከትቶ በመቆየት አገዛዙ በመፈፀም ላይ ባለው የመብት ረገጣ ላይ ያለውን ተቃውሞ እንዲያሰማ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ አቀረቡ። የኢሕአዴግ መሪዎች ከቤቱ አልወጣም ያለን ሕዝብ በየጓዳው እየገቡ መረሸን በማይችሉበት ሁኔታ በዚህ እርምጃ ሰበብ ምን ያህል መጋለጥ እንደሚመጣ በመረዳታቸው ይኸን ሕዝባዊ ትግል አዘናግተውና ጊዜ ጠብቀው ለመበተን ለተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች የእጅ አዙር የእንደራደር ጥሪ አቀረቡ። ቅንጅቱና ኅብረቱ ይኸንኑ የድርድር ጥሪ በቅን መንፈስ በመቀበልና ለሰላም ዳግም ዕድል ለመስጠት ሲሉ የተጠራውን የሦስት ቀናት የቤት መቆየት ጥሪ ሰረዙ።

ኅብረቱ ይኸን የኢሕአዴግ መሪዎች የተቀበሉትን የድርድር ጥሪ በሕዝብ ተጋድሎ እንደተገኘ ድል ይቆጥረዋል። ለመደራደረም ዝግጁ ነው። ነገር ግን ይኸ የተወሰኑ መሪዎች በዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ አጋፋሪነት ከኢሕአዴግ ጋር የሚያደርጉት ድርድር በምንም ዓይነትና መንገድ የሕዝቡን ትግል የሚተካ ትግል አይሆንም።

ሁለት መሠረታዊ ቁም ነገሮችን ሁሉም ሊገነዘባቸው ይገባል።
አንደኛ ዛሬ እዚህ የድል ምዕራፍ የተደረሰው ሕዝባችን በንፁሕ ልጆቹ ደም በከፈለው መሰዋእትነት፥ በያለበት በመላ አገሪቱ ከመሐሉ ሆነው በተዋደቁ ልጆቹ ንቁ ተሳትፎና ተጋድሎ ነው።
ሁለተኛ ድርጅቶቹ መገንዘብ ያለብን አሁን ካለንበት የድልና የትግል ምዕራፍ አንዲትም ብትሆን የወደፊት እርምጃ ማድረግ የምንችለው እዚህ ያደረሰንን ሕዝብና በያለበት ያሉ ታጋይ ልጆቹን እንደያዝን ስንቀጥል እንጂ በምንም ምክንያት ይሁን በምን እነሱን ተክተን በነሱ ቦታ ትግሉን እኛ ከኢሕአዴግ ጋር በተናጠል እናካሂደዋለን እያልን አጉል ስንግደረደር አይደለም።

ስለሆነም አንደኛ መስከረም 21 ቀን 1998 በተቃዋሚ ድርጅቶች (ቅንጅትና ኅብረት) እና በኢሕአዴግ መካከል ለድርድር ለመስማማት የተሰጠውን መግለጫ መንፈሱን ጨርሶ በማዛባት የመንግሥት ዜና ማሰራጫዎች ተቃዋሚዎች ፓርላማ ለመግባት ተስማምተዋል

በሚል ያሰራጩት ዜና ከእውነት የራቀና የኅብረቱ አቋምም፥ ግንዛቤም ሆነ አስተሳሰብ አለመሆኑን እንገልጻለን።

ከኢሕአዴግ ጋር የምንደራደርባቸው ነጥቦች የፖለቲካ አስረኞች እንዲፈቱ፥ ታጋዮችን ማዋከብ እንዲቆም፥ የመገናኛ ብዙኃን ለሁሉም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ክፍት እንዲሆኑ ወዘተ.. የሚሉትን ቢጨምርም ከማንኛውም ተጨማሪ የመደራደሪያ ነጥብ በፊት የተጭብረበረውን የሕዝብ ድምፅ ለማስመለስ ሰላማዊ መፍትሔ እንዲሆን የቀረበው የብሔራዊ የአንድነት የሽግግር መንግሥት ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል።

የኢሕአዴግ መሪዎች በእርግጥ ቀውሱን በሰለማዊና በዴሞክራሲያዊ ዘዴ ለመፍታት ይፈልጉ አንደሆነ ወይስ ደግሞ ለጊዜው በድርድር ሰበብ የኅብረተሰቡን የትግል መንፈስ ለማላላት የተጠነሰሰ ጊዜ መግዣ ሴራ መሆኑ አንዲለይ ሁለት ቀላል ነጥቦችን ለድርድ እናቀርባለን።

አንደኛ በሕገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ዜጎች የመሰብሰብ መብት እያላቸው የአዳራሽ ጉባዔን እስከ መከልከል የደረሰ መንግሥት ከዚች መሠረታዊ መብት አልፎ የሚጠየቀውን ሌላ የሕዝብ ጉዳይ በፀጋ ይቀበላል የሚል እምነት ስለሌለንና ከሁሉም በላይ ደግሞ የፖለቲካ መሪዎች የሚደራደሩባቸው መሠረታዊ ነጥቦች የሕዝብና የኅብረተሰቡን ቅባሎት መጀመሪያ ማግኘታቸው መረጋገጥ ስላለበት ቀደም ሲል የታሰበውና በኢሕአዴግ መሪዎች ዓይን ያወጣ ሕገ-ወጥ እርምጃ የተደናቀፈው "የሰለም የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞከራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ "ን እንደገና ስንጠራ ይኸን ጉባዔ ዳግም ላለማደናቀፍ ቃል እንዲገቡ፤

ሁለተኛ አሁንም የትግላችን ስልት ከሕዝባችን ጋር (ሕዝባችንን ይዘን) የሚል በመሆኑ ጉባዔው ለሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሕዝባችን ያለውን ድጋፍ ለመግለፅ እንዲችል በጉባዔው ማግስት በመላ የአገሪቱ ክፍል ለማዘጋጀት ላሰብነው ሰልፍ እንቅፋት ከመደንቀር ይልቅ ለሚመለከታቸው የመንግሥት ክፍሎች ሁሉ የትብብር መመሪያ እንዲያስተላልፍና ይኸ ሰልፍ ሕዝባችን ባስለመደንና በዓለም ፊት ባስመሰከረው ጨዋነት እንዳይካሄድ ምንም ዓይነት አደናቃፊ እርምጃዎች ላለመውሰድ ቃል እንዲገቡ፥ ይኸም በገዥው ፓርቲና መንግሥት መሪ በአቶ መለስ ዜናዊ አማካይነት በመገናኛ ብዙኃን ለተቃዋሚ ድርጅቶች፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ በግልጽ ከተገለጸ ድርድሩን ተቀብለን ለመቀጠል ችግር የለብንም፥ የምንፈልገውና የምንደግፈውም ይሆናል። ከዚህ ውጭ ሕዝባችንንና ታጋይ ልጆቹን ወደ ጎን በተወ መልክ ይካሄድ የሚባል የጓዳ ድርድር ራስን ለማንበርከክ ማደራጀት ስለሆነ ኢዴኃኅ የሚስማማበት አይሆንም።
<u>በመሆኑም የኢሕአዴግ መንግሥት በዚህ ጥሪ መሠረት ተደራድሮ አዎንታዊ መልስ የማይሰጥ ከሆነ ሃቀኛ ድርድር ተስፋ እንደሌለው ተወስዶ፤ ላልተወሰነ ጊዜ ተላልፎ የነበረው ሕዝቡ በገዥው ፓርቲ ላይ ያለውን ተቃውሞ እንዲያሳይ የተደረገው ጥሪና ለሌሎች ሰላማዊና ሕጋዊ የትግል ዘዴዎች ወለም-ዘለም በሌለበት ሁኔታና በአዲስ መልክ ዳግም ድርድር ቢጀመር እንኳ ትግሉ ሳይቋረጥ እየታገሉ ለመደራደር በሚያስኬድ መልክ ብቻ እንደገና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊጠራ እንደሚችል አውቆ ሕዘባችን በተጠንቀቅ እንዲጠባበቅ ጥሪያችንን በከፍተኛ አክብሮት እናስተላልፋለን።</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነቱ የተነጠቁ መብቶቹን ያስከብራል!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ኢዴኃኅ
መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

የ ኃውሬይ